# ታማኝነትና ፖለቲካ በኢትዮጵያ፡ ታማኝነት ለማን? ታማኝነት ለምን?[1]

**ብርሃኑ ነጋ[2]**

**መግቢያ**

በሰሞኑ በአሜሪካ በኦባማና በክሊንተን መሀከል የዴሞክራሲያዊ ፓርቲውን ወክሎ ለፕሬዜዳንታዊ ምርጫው እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ ከሚደረገው አጉዋጊ ፉክክርም በላይ ሁሉንም የአሜሪካ መገናኛ ብዙሀንና የአገሬውንም ህዝብ ቀልብ የተቆጣጠረውና በአገሪቱ ትላልቅ የፖለቲካና የሚዲያ ሰዎች መሀከል ከፍተኛ ክርክር የቀሰቀሰው ትልቁ ወሬ የቀድሞው የፕሬዜዳንት ቡሽ የሚዲያ ፀሀፊ ሆኖ በተለይ የኢራቅን ጦርነት ለአሜሪካ ህዝብ ለመሸጥ ትልቅ ሚና የተጫወተው ስኮት ማክሊላን የፃፈው አዲስ መፅሀፍ ጉዳይ ነው። ጉዳዩ በአጭሩ እንዲህ ነው። ስኮት ማክሊላን በቴክሳስ ክፍለ ሀገር ውስጥ ከሚኖሩና ለሪፑብሊካን ፓርቲው ከፍተኛና የእድሜ ልክ ታማኝነት ካላቸው ቤተሰቦች የተወለደና እሱም ለዚህ ፓርቲ ከፍተኛ ታማኝነትን ይዞ ያደገ ሰው ነው። ከዚያም በላይ ቡሽ ገና የቴክሳስ አገረ ገዢ ሆኖ እያለ በ1999 ዓ.ም. ነበር የቡሽን ቡድን የተቀላቀለውና ለቡሽ መስራት የጀመረው።

የሁዋይት ሀውስ የሚዲያ ሀላፊ ሆኖ በሚሰራበት ጊዜ በኢራቅ ጉዳይም ሆነ በሌሎች የቡሽ አስተዳደር ቅሌቶች ላይ (ለምሳሌ በአሳፋሪ ሁኔታ ካርል ሮቭና እስኩተር ሊቢ የተባሉ የቡሽ ከፍተኛ አማካሪዎች በኢራቅ የመረጃ ጉዳይ ልዩነት የተነሳ በሚስጥር የምትሰራ የስለላ ድርጅት አባልን ስም ለጋዜጠኞች የነገሩበት እንደ ክህደት የሚቆጠር ወንጀል) ማክሊላን አስተዳደሩን ወክሎ ለሚዲያ መረጃ የሚሰጠው እሱ ስለነበር ከሚዲያው የሚመጡትንም ጥያቄዎች የሚመልሰው እሱው ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ አስተዳደሩን በአሜሪካ ህዝብ ፊት እንዳይሳጣ ለመከላከልና ጦርነቱን ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ሙሉ ለሙሉ እውነት ያልሆኑ ብዙ ነገሮችን በአስተዳደሩ ስም ለህዝቡ ተናግሮአል። እንደማክሊላን አባባል ከሆነ እነኝህ የተናገራቸው ነገሮች ሀሰት መሆናቸውን በጊዜው አያውቅም ነበር። እሱም እንደሌላው በለት ተቀን የፖለቲካ ስሌት በመነዳት በጊዜው ለፖለቲካው የሚጠቅመውን ነገር ነበር ሲያደርግ የነበረው። የሁዋይት ሀውስ ስራውን በፈቃዱ ከለቀቀ በሁዋላ በቡሽ አስተዳደር ውስጥ በሚሰራበት ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ እውነቱን ለአሜሪካ ህዝብ መናገር አለብኝ ከሚል ነው እንግዲህ ይህንን እጅግ አወዛጋቢ የሆነ መፅሀፉን የፃፈው። በዚህ መፅሀፍ ውስጥ ቡሽን እራሱን እንደሰውና እንደፕሬዜዳንት፣ አስተዳደሩንም እንደ አስተዳደር በብዙ ጉዳዮች ላይ እያብጠለጠለ ተችቶአቸዋል። ይህ መፅሀፍ ለቡሽም ሆነ ለሪፑብሊካን ፓርቲው በጣም አሳፋሪ የሆነና በመጪውም የፕሬዜዳንታዊ ምርጫ የሪፑብሊካን ፓርቲውን ክፉኛ ሊጎዳ እንደሚችል ሀያስያን በሰፊው ይናገራሉ።

ዛሬ ልናገርበት ከፈለግሁት እርእስ ጋር የሚገናኘው ጉዳይ ያለው ከላይ ባነሳሁዋቸው ጭብጦች ላይ ሳይሆን መፅሀፉ ከወጣ በሁዋላ ያስነሳው ውዝግብ ላይ ነው። መፅሀፉ እንደወጣ በጣም በሚገርም ሁኔታ የሪፐብሊካን ፓርቲው ከፍተኛ አባላትና ፓርቲውን የሚደግፉ ኤክስፐርቶች ከአንድ ማእከል የተላለፈ የማውገዢያ ፅሁፍ የሚያነቡ በሚመስል መልኩ እየተረባረቡ ማክሊላንን ሲያወግዙት ሰንብተዋል። እሱም በየሚዲያው ላይ እየዞረ እራሱን ሲከላከል ሰንብቱዋል። የማክሊላን ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡትን መቃወሚያና የእሱንም መልስ ዛሬ ልናገርበት ካሰብኩት ዕርእስ ጋር በጣም ስለሚገናኝ ጠቅለል አድርጌ በአጭሩ ላቅርበው። በተቃዋሚዎቹ ሀሳብ ልጀምር

- ማክሊላን በመፅሀፉ ላይ ያቀረባቸው አስተያየቶች ክርክሩ በሚካሄድበት ጊዜ የያዛቸው አይደሉም፣ በዚያን ጊዜ ይዞአቸው እንደነበረ የሚያሳይ ምንም ምልክት የለም። ስለዚህ ስራውን ከለቀቀ በሁዋላ መፅሀፍ ለመሸጥ ብሎ የሚለው ካልሆነ በስተቀር ከምር ሊወሰድ የሚችል አይደለም።

---

[1] እዚህ ላይ ታማኝነት የሚለውን ቃል በእንግሊዘኛ (loyality) የሚለውን ትርጉም እንዲይዝ ነው የተጠቀምኩበት:: የዚህ ቃል ተቃራኒ ክህደት ወይንም ከሀዲነት የሚለው ነው ማለት ነው።

[2] በለንደን የሰኔ 1997 ዓ.ም. ግድያንና በጊዜው የሞቱትን ሰማእታት ለመዘከር በተደረገ የኢትዮጵያውያን ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር። ሰኔ 1፣ 200 ዓ.ም።

- *ማክሊላን እንዲህ አይነት ከሀዲ ሰው አይደለም፡፡ አንድ የሆነው ነገር አለ፡፡ ምናልባትም የመፅሀፉ አሳታሚዎች መፅሀፉ እንዲሸጥላቸው ብለው ገፋፍተውት ካልሆነ በስተቀር ይህ የምናውቀውና እናከብረው የነበረ ባልደረባችን እንዲህ አይነት ክህደት በራሱ ተነሳሽነት ይፈፅማል ብለን ለማመን ያስቸግረናል፡፡ ያደረገው ድርጊት ግን በማንም ተገፋፍቶ ይሁን በማን ምንም ምህረት የማይደረግለት ክህደት ነው (ማለትም ድርጅቱንና አለቃውን)፤ ያሳየውም እንደ ይሁዳ ከሀዲ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ አይነት ከሀዲ ደግሞ ከምር ሊወሰድ አይገባውም፡፡*

- *የቀድሞው የአሜሪካ ሴናተር ቦብ ዶል በተለመደው የሾለ ምላሱ ያለው ደግሞ፡ ይህ ሰው ቅሌታምና ወራዳ ሰው ነው፡፡ ከስልጣን ተጠግቶ ባለበት ጊዜ ይህ አሁን የሚለው ነገር ሲፈፀም እያየ ችግሩን ለመከላከልና ይህ ሁሉ አደጋ ከመድረሱ በፊት ለማስቆም እንደመሞከርና ካልቻለ ደግሞ ከህሊናዬ ጋር ከምጣላ ስራውን እለቃለሁ ብሎ እንደመልቀቅ፤ ከስልጣን የሚገኘውን ጥቅም ላለማጣት ዝም ብሎ ከርሞ አሁን በዚያ ስልጣኑ ጊዜ ያገኘውን መረጃ ገንዘብ ለማግኘት ሲል የሚፅፍ ሰው እራስ ወዳድና ህሊና ቢስ ከመሆን በቀር ሌላ ምንም ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ማክሊላን አሳዛኝና ከሀዲ ፍጡር ነው፡፡...ወዘተ*

*በሌላ በኩል ደግሞ ማክሊላን እራሱም ሆነ የሚደግፉት ሰዎች የሚሉት፡*

- *አሁንም ቢሆን ቡሽን የማያደንቅበት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ግን የቡሽ አስተዳደር የሰራቸው ብዙ ስህተቶች ለህዝቡ በግልፅ መነገር አለባቸው፡፡ ለአንድ ድርጅት ያለኝ ድጋፍና ታማኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ የእኔ ወይንም የማንኛውም አሜሪካዊ የመጨረሻው ታማኝነት ለአንድ ግለሰብ ወይንም የፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን ለእውነትና ለአሜሪካ ህዝብ ነው፡፡ የዚህ እውነት መውጣት ደግሞ አገራችንንና ህዝቡዋን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ‹በግለሰብና ድርጅት ታማኝነት› ምክንያት የአገርን ጥቅም ወደሁዋላ ማስቀረት ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲያውም ከሀዲነት የሚሆነው እሱ ነው፡፡*

- *አብዛኛው አሁን ሀሰት መሆኑን ያወቅሁት ነገር በጊዜው እውነት ነው ብዬ የተቀበልኩት ነገር ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ባለስልጣኖች እኔንም ነበር ፊት ለፊት የዋሹኝ፡፡ ስለዚህም እንደሌላው አሜሪካዊ ሁሉ እኔም ነበር የተታለልኩት፡፡ ይህንን ካወቅሁ በሁዋላም ነበር ከዚያ አስተዳደር ለመልቀቅ የወሰንኩት፡፡ አሁን እውነቱን የተናገርኩትም በሁዋላ ያወቅሁት ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡ በዋሽንግተን ያለው ‹ማሸነፍን ብቻ ማእከል ያደረገ› መጥፎ የፖለቲካ ባህል ምን ያህል ስር የሰደደ አስቀያሚና ከፍተኛ የሞራል ድክመት የሚንፀባረቅበት መሆኑን ከራሴ ልምድ ከተረዳሁ በሁዋላ ይህንን ለህዝቡ ሳይናገሩ ዝም ብሎ መቀመጥ በሞራልም በዜግነትም የሚያስጠይቅ ነው ብዬ ስለማምን ነው አሁን እውነቱን የምናገረው፡፡[3]*

---

*[3] እዚህ ላይ ይህን ‹ታማኝነትና ክህደትን› በሚመለከት የህዝብ ጥቅም ወይንም የህዝብ ፍላጎት የሚለው ነገር ከቁጥር ጋር በማያያዝ ስህተት እንዳይፈጠር አጭር ማብራሪያ ማቅረቡ ይጠቅማል፡፡ በተለምዶ አነጋገር የህዝብ ጥቅም የሚለው ማህበረሰቡን በጥቅሉ ለማመልከት እንጂ በቁጥር የብዙሀኑን ጥቅም ማስጠበቅ ከሚል ጋር የተያያዘ አይደለም፤ ምንም እንኩዋን ሁለቱ አንድ አይነት የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች ብዙ ጊዜ እንደሚከሰቱ የታወቀ ቢሆንምና በዴሞክራሲያዊ ስርአት አብዛኛው ለወሰነው ሁሉም ተገዢ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩ የሚካድ ባይሆንም፣ በእንዲህ አይነት ጉዳይ ግን ለአገርና ለህዝብ ታማኝነት ብዙሀኑ የሚለውን በመቃወም ሊገለፅም እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡ ለምሳሌ በአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ አንድ በህዝብ የተመረጠ መንግስት አንድን አናሳ ዘውጌ ማህበረሰብ ለማጥፋት ሆን ብሎ ቢንቀሳቀስና ይህም በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት ተቀባይነት ወይንም ድጋፍ ቢኖረው (ለምሳሌ በናዚ ጀርመን፤ወይንም በሩዋንዳ) ይህንን የአብዛኛውን ህዝብ ፍላጎት (እብደት) መቃወም በምንም አይነት ‹ህዝቡን መክዳት› ሆኖ ሊወሰድ ወይንም ደግሞ ይህንን መደገፍ ለህዝብ ታማኝነትን መግለጫ ሆኖ ሊወሰድ አይገባም፡፡ እንዲያውም ይህንን አይነት ‹ማህበረሰባዊ እብደት› አጠንክሮ መቃወምና መታገል ነው እውነተኛ የአገር ወዳድነትና የህዝብ ታማኝነት ሆኖ መወሰድ ያለበት፡፡ ምክንያቱም የዚህ አይነቱ ሰው ታማኝነት ለማህበረሰቡ ዘላቂ ጥቅምና ቁዋሚ እሴቶች የቆመ ታማኝነት ስለሚሆን፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ በፖለቲካ ሀይሎች አማካኝነት ወይንም ገፋፊነት ብቻ ሳይሆን ለምሳሌ እንደ ሀይማኖት ያሉ ከፍተኛ የሞራል ገዢ መሬት ላይ ሆነው የሚሰብኩ አካሎች ማህበረሰብን የሞራል ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሊከቱት እንደሚችሉ በታሪክ በተደጋጋሚ የታየ ነው፡፡ በእንዲህ አይነት ጊዜም ዜጎች ማህበረሰቡን መርጎ የያዙትን ከሀይማኖት ውጪ ያሉ የሞራል እሴቶች በሀይማኖት ስምም ለመሸርሸር የሚደረግን ሙከራ መቃወም ለአገርና ለማህበረሰቡ ያለን ከፍተኛ ታማኝነት የሚገለፅበት የሞራል እሴት ተደርጎ የሚወሰደው፡፡ ከዚህ አንፃር የቀኝ ክንፍ የክርስትና አክራሪዎች የአሜሪካንን ማህበረሰብ እንዴት*

*ይህም ሆኖ ግን አውቄም ሆነ ባለማወቅ የአሜሪካንን ህዝብ በማሳሳቴ በጣም አዝናለሁ። ሌሎች ደጋፊዎቼ ደግሞ፤*

- *ማክሊላን ያደረገውን ቀደም ብሎና በጊዜው ቢያደርገው ጥሩ ነበር። አሁንም ቢሆን ይህንን በማድረጉ የሚደርስበትን የስድብ ውርጅብኝ እያወቀ፤ ከቀድሞ ጉዋደኞቹና ከፖለቲካ ድርጅቱ ጋር ሁሉ እንደሚቆራረጥ እያወቀ ይህንን ለማድረግ የሞራል ድፍረት ማግኘቱ የሚያስመሰግነው ነው፤ የሁሉም ለአገርና ለህዝብ አስባለሁ የሚል ሰው ታማኝነትም መሆን ያለበት ለእውነቱና ለህዝቡ ነው። ለድርጅትና ለግለሰብ መሆን የለበትም...ወዘተ።*

በዚህ አንድ እውነተኛና ጊዜያዊ ምሳሌ ውስጥ ታጭቀው የሚገኙት መአት መሰረታዊ የፖለቲካና የባህርይ ጥያቄዎች አሉ። የኢትዮጵያችንን የቀደምትም ሆነ የአሁኑን ፖለቲካ መያዥያ መጨበጫ እንዲጠፋው ካደረጉት ነገሮች አንዱ በእንደዚህ አይነት የእያንዳንዳችንን ማንነት፤ የውስጥ የሞራልና የግብረገብነት እሴቶቻችንን የሚነኩ ነገሮች ከጋራ ማህበራዊ ማንነታችንና የጋራችን ናቸው ከምንላቸው እሴቶቻችን ጋር ሲገናኙና ሲጋጩ የሚፈጠረው ቀላል ያልሆነ የስነአእምሮና የሞራል ትርምስ ይመስለኛል።

እንደሚታወቀው ታማኝነት በራሱ በጣም ተፈላጊነት ያለው ትልቅ እሴት ነው። ለቤተሰብ፤ለወዳጅና ለጉዋደኛ በደጉ ጊዜም ሆነ በችግር ጊዜ ታማኝ መሆን፤ በተለይ በጥቃት ጊዜ ለእነኝህ ሰዎች መድረስና አለሁ ማለት በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያለው ሞራላዊ እሴት ነው። ይህ የታማኝነት እሴት ግን በተለይ በሞራል መለኪያ ሲለካ ከሌሎች የዚያኑ ያክል አስፈላጊ ከሚባሉ እሴቶች ጋር ሊጋጭ ይችላል። ያን ጊዜ ህሊና ባለው ሰው ላይ የሚፈጥረው የውስጥ ግጭት ቀላል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ግጭቱ ለዚያ ሰው ያለን ታማኝነት ለሌላ ሰው ካለን ታማኝነት ጋር ሊሆን ይችላል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ለግለሰብ ካለን ታማኝነት ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ወይንም ደግሞ በጣም ለምናምንበት መርህ ካለን ታማኝነት ጋር ይሆናል። ምንም ሆነ ምን ግን እንደዚህ አይነት ግጭት ሲፈጠር ውስጣችንን ማተራመሱ አይቀርም። ዋናው ነጥብ ግን እንዲህ አይነቱን የውስጥ ትርምስ እንዴት እንፈታዋለን? ለየትኛው ያለን ታማኝነት ነው ቅድሚያ ሊኖረው የሚገባው? የሚለው ላይ ነው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ግጭቱ ያለው ታማኝ በመሆንና ባለመሆን ላይ ሳይሆን በሞራል ደረጃ የላቀ ተቀባይነት ያለው ትልቁ ታማኝነት የት ላይ ነው ያለው የሚለው ላይ ነው። ከላይ የጠቀስኩት የማክሊላን ምሳሌ ይዞልን የቀረበው ይህን ጥያቄ ነው። በግለሰብ ደረጃ እንዲህ አይነት ጥያቄ ሊቀሰቅስ የሚችለውን የውስጥ ትርምስ ስእላዊ በሆነ መንገድ ሊገልፅ የሚችል አንድ ሌላ እውነተኛ ምሳሌ ላክልና ወደ ዋናው ነጥቤ ልመለስ። ከጥቂት አመታት በፊት አዲስ አበባ እያለሁ የገጠመኝ አሳዛኝ አጋጣሚ ነው። አንድ ጥጋቡን መቆጣጠር ያልቻለ ጎረምሳ ሀብታም በንግድ የሚገናኘውን አንድ ጉዋደኛውን አብረው ሲጠጡ ካመሹ በኑዋላ ለተጨማሪ መጠጥ እቤት እንሂድ ብሎ እቤቱ ወስዶ በአሰቃቂ ሁኔታ ይገድልና በነፍስ ተከሶ ይታሰራል። ይህ ነፍስ ያጠፋ ሰው በከፍተኛ ገንዘብ ብርታት (በዚህ ጉዳይ ስለተበላው ጉቦ ፍርድ ቤት አካባቢ እንደ ተአምር ነው የሚወራው) 7 አመት ብቻ ይፈረድበታል። የሙዋች ቤተሰቦች በራሳቸው ባለገንዘቦች ነበሩና ይህንን አሳዛኝ ፍርድ ለማስቀየር ይግባኝ ይላሉ። በዚህን ጊዜ ነበር አንድ በጣም የምወደውና የማከብረው ለተባበሩት መንግስታት ይሰራ የነበረና ጡረታ የወጣ ግን ጥሩ ኑሮ ያለው ሽምግል ያለ ሰው ቢሮዬ ደውሎ ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሀለሁ ብሎኝ ቀጠሮ ሰጥቼው ቢሮዬ የመጣው። ይህ ሰው የመጣው በልጁ ተልኮ ነው። ልጁ ከገዳዩ

---

*እያመሱት እንዳለና ዜጎች ለምን ይህንን መሰሪ በሀይማኖት ስም የመጣ የፋሽስት ሀይል መታገል እንዳለባቸው ክሪስ ሄጅስ የተባለ ፀሀፊ የተናገረውን መጥቀሱ ለማለት የፈለግሁትን በተሸለ ሳያብራራው አይቀርምና ልጥቀሰው፡*
*" አሜሪካ ሁሉም ዜጋ እንዴት እንደሚኖርና እንዴት እንደሚተዳደር ድምፁ የሚሰማበት አገር ነች። ሆኖም ይህንን መሰረታዊ እሴት ገና ሙሉ ለሙሉ አልተገበርነውም በቻ ሳይሆን ምናልባትም መቼም ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ላናደርገው እንችላለን። ግን ጤነኛ አገር ሆነን መቀጠል አለመቀጠላችንን የሚወስነው ይህንን እሴት ሙሉ ለሙሉ ለማግኘት የምናደርገው ያላሰለሰ ጥረት ነው። አንዳንድ ጊዜ ጠንካራ የሞራል አቋዋም መያዝ (በነገራችን ላይ ይህ የአገር ወዳድነት ትልቁ መገለጫው ነው) ማለት ማህበረሰባችንን አልፎም አገራችንን አንኩዋሰን ማየት ማለት ሊሆን ይችላል። ግን ሬይሞንድ ኔቡር እንዳለው ለማህበረሰባችን ወይንም ሳገራችን ያለን ታማኝነት በሞራል መለኪያ ተቀባይነት የሚኖረው ያሉን የሞራል እሴቶች ማህበረሰባችን ካሉትም የሞራል እሴቶች ሰፋ ያሉ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው።" ክሪስ ሔጅስ.* ***የአሜሪካ ፋሽስቶች፡ የቀኝ ክንፍ የክርስትና አክራሪዎችና በአሜሪካ ላይ የከፈቱት ጦርነት.*** *ኒው ዮርክ፣ ፍሪ ፕሬስ፣* 2006 *ዓ.ም. ገፅ.* 10.

ወንድሞችና ቤተሰቦች ጋር በጣም ቅርበት አለው፡፡ የተለያዩ የንግድ ስራዎችም አብረው ይሰራሉ፡፡ ለነኝህ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ታማኝነት አለው፡፡ እኔ ጋ የመጣው አባትየው ደግሞ ልጁን በጣም ስለሚወደው ለልጁ ታማኝነት አለው፡፡ እስከአሁን ምክንያቱን በማላውቀው ነገር ይህንን ጉዳይ ባለበት ለማስቆም የሚችል አንድ ሰው የእኔ ከፍተኛ ወዳጅ ነው ብለው ያምናሉ (የሚገርመው የተባለውን ባለስልጣን እኔ እንዲያውም ስሙንም ሰምቼው አላውቅም)፡፡ ለማንኛውም ልጅየው በአባቱ በኩል እኔ ጋር የመጣው ይህንን ባለስልጣን እኔ አናግሬው በገዳዩ ላይ ያለውን የፍርድ (የይግባኝ) ሂደት ባለበት ለማስቆምና ገዳዩ በመጀመሪያው ፍርድ መሰረት (አመክሮ ሲቀነስለት ከአምስት አመት በታች ነው የሚታሰረው) ጊዜውን እየጨረሰ ስለሆነ ከእስር እንዲለቀቅ ፈልጎ ነው፡፡ አባትየው ይህን ጥያቄ ሲጠይቀኝ ሙሉ ለሙሉ ጥሩ ስሜት እየተሰማው እንዳልሆነ ያስታውቃል፡፡ እኔም በአባትየው ጥያቄ ትንሽ የተረበሽኩ መሆኔ ያስታውቃል መሰለኝ ‹እንደው በጣም አስቸገርኩህ› የሚል ነገር አባትየው አብዝቶአል፡፡ ጥያቄውን አቅርቦ ሲጨርስ በመጀመሪያ የጠየቅሁት ነገር አንተ ይህንን ፍርድ የማስቆም አቅሙ ቢኖርህ ታስቆመው ነበር ወይ; የሚለውን ጥያቄ ነበር፡፡ ሰውየው ህሊና ያለው ሰው ስለነበር ልክ ይህን ስናገር ከመቀመጫው ተነስቶ በጣም አዝኖ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ ልጁን ለማስደሰት ብሎ ወይም ለልጁ ባለው ታማኝነት ምክንያት ሁሉንም ማህበረሰብ ለሚመለከተው ለፍትህ ወገንተኛ አለመሆኑ በጣም ነበር የቆጨው፡፡ አንድም ተጨማሪ ቃል ሳይተነፍስ ነበር ቢሮዬን ትቶ የወጣው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በተገናኘን ቁጥር በጣም ስለሚያፍረኝ እንደበፊቱ ለመሆን አልቻለም፡፡ ይህ ምሳሌ ያስነሳውን የሞራልና የታማኝነት ጭንቀት በደንብ ለማየት በሰውየው ላይ ከመፍረዳችሁ በፊት እስኪ ገዳዩ የእናንተ ልጅ ወይንም ወንድም እንደሆነ አድርጋችሁ እዩት፡፡ ታማኝነታችሁ ለማን ነበር የሚሆነው?

ይህ ምሳሌ ለአገራችን ፖለቲካ፤ በማህበረሰባችን ውስጥ ትልቅ ቦታ ለሚሰጠው የታማኝነት ባህርይና ተቀራራቢነት ላላቸው ሌሎች እሴቶች፤ በተለይም ደግሞ እንዲመሰረት ለምንፈልገው ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካና እሱም ግድ ለሚለው ማህበራዊ ባህርይ ብዙ ትርጉም ስላለው ለዛሬ ውይይት ላተኩርበት መርጫለሁ፡፡ በተለይ ላተኩርበት የፈለግሁት ደግሞ ለድርጅት በሚኖር ታማኝነትና በአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ወይንም ማህበረሰቡን ይጠቅማል ለሚል አላማ ወይም መርህ ላይ በሚኖር ታማኝነት መሀከል ባለው ልዩነት ዙሪያ ይሆናል፡፡ ይህ በከፍተኛ ደረጃ ስሜትን ለመቀስቀስ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ግን በደንብ ካላሰብንበትና በጉዳዩ ላይ የጠራ አመለካከት ካልያዝን ስሜታዊነት ብቻውን አጠቃላይ የዴሞክራሲ ትግሉን ችግር ውስጥ የሚከት ብሎም መከራችንን የሚያራዝም ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ከምር ልንወያይበት የሚገባው፡፡

ወደዚያ ውይይት ውስጥ ከመግባቴ በፊት ግን የተለመደ ምስጋናዬን ላስቀድም፡፡ በለንደን የሚገኘው የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት በዚህ የሰኔ ሰማእታት ቀን በአል ላይ እንድመጣ የጋበዘኝ እኔና ጉዋደኞቼ ከቅንጅቱ መውጣታችንን ከማስታወቃችን ቀደም ብሎ ነበር፡፡ እኛ ቅንጅትን ከለቀቅን በሁዋላ፤ ከዚያም በላይ ለትግሉ ይጠቅማል ብለን ያሰብነውን አዲስ መንገድ ከቅንጅት ተለይተን ከቀየስን በሁዋላ ተመልሶ የቅንጅት በአል ላይ መገኘት በሁሉም ላይ ሊፈጥር የሚችለውን አለመመቸት በመገንዘብ ከፕሮግራሙ እንድወጣ ጠይቄ ነበር፡፡ አዘጋጆቹ የሰጡኝ መልስ ግን፤ ታማኝነታቸው በአገራቸው ለሚካሄደው የዴሞክራሲ ትግል መሆኑንና ድርጅቱን መልቀቄ ወይንም ሌላ ድርጅት ውስጥ መግባቴ ይህንን ንግግር ለማድረግ ሊከለክለኝ እንደማይገባ ነበር፡፡ በዚህ መልሳቸው በመገረምና በራሴ ውሳኔ ልገኝ አልገኝ የሚለውን ሀሳብ ሳብላላ ነበር በዚያኑ ቀን ይህንን በአል በዋሽንግተን ዲ.ሲ የሚያከብረው የቅንጅት የድጋፍ ሰጪ አካል በበአሉ ላይ እንድገኝ የጋበዘኝ፡፡ ይህ ግብዣ የተደረገው ግንቦት 7 ከተቋቋቋመም በሁዋላ መሆኑ ደግሞ በውስጤ ያሳደረው የደስታ ስሜት ከፍ ያለ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለካ ከዚህ ሁሉ ትርምስም በሁዋላ የአገራችን የዴሞክራሲ ትግል እየተዳከመ ሳይሆን የበለጠ ጥልቀት እያገኘ እየሄደ ነው የሚል ትልቅ ተስፋና ኩራት ነበር የተሰማኝ፡፡ ስለዚህም ነው እናንተን የለንደን ጋባዦቼን ብቻ ሳይሆን ምንም እንኩዋን በአካል ሁለት ቦታ መሆን ባልችልም በመንፈስ ግን በዋሽንግተን ከሚገኙትም የዴሞክራሲ ወገንተኞች ጋር አብሬ በመሆኔ ሁለታችሁንም በጣም ማመስገን የምፈልገው፡፡ ሌሎችም አድማጮቼ በዚህ ስብሰባ ላይ ተገኝታችሁ በጋራ አገራችን ጉዳይ ላይ ለመምከር፤ ለዴሞክራሲ ሲሉ የተሰዉትን ወገኖቻችንን ለመዘከር ለተገኛችሁት እግዚአብሄር ያክብርልኝ እላለሁ፡፡

## የፖለቲካ ታማኝነት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ

በአገራችን የአጭር ጊዜ ዘመናዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች ለድርጅታቸው ያላቸው ታማኝነት በጣም ጠንካራ መሆኑን ቢያንስ ላለፉት አርባ አመታት በስፋት ያየነው ነው፡፡ በመንግስት ታጣቂዎች በጥይት ተመትተው እየሞቱ እያሉ የድርጅታቸውን ስም በደማቸው እየፃፉ ካለፉት ወይንም የመንግስት ሰቆቃ ምናልባት የድርጅታቸውን ሚስጥር እንዳያስወጣቸው በመንግስት አፋኞች በተያዙ ጊዜ የሳይናይድ ኪኒን ውጠው እራሳቸውን የገደሉ ብርቅዬ የኢህአፓ ወጣቶች፤ በተደጋጋሚ አሰቃቂ ሰቆቃ እየተፈፀመባቸው የድርጅታቸውን ሚስጥር ሳያወጡ ካለፉት የኦነግ ተጋዳዮች፤ የህዝብ ድምፅ አናስነጥቅም ብለው በአደባባይ ወጥተው እስከ አፍንጫው የታጠቀን ሀይል በድንጋይ ከገጠሙት የቅንጅት ደጋፊዎች ድረስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብዙ የድርጅት ታማኝ ጀግኖችን አሳይቶናል፡፡ የታማኝነት እጥረት ኖሮብን አያውቅም፡፡[4] ምናልባት በዚህ ዙሪያ በተለይ በቀደምቱ ትግል ወቅት እንደችግር ሊታይ የሚችለው የድርጅታዊ ታማኝነት ብዛት ከአጠቃላይ አገራዊ ጥቅም ጋር ሊጋጭ የሚችልበትን ሁኔታ በጉልህ ማሳየቱ ነው፡፡

በ1960 ዎቹ ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል አንድ ልዩ ምልክቱ በተቀናቃኝ ወገኖች መሀከል ያለው ርዕዮተ አለማዊ አክራሪነት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም ድርጅቶች ማለት ይቻላል ምንም ለጥርጣሬ በር ያልከፈተ እርግጠኛ አመለካከት ነበራቸው፡፡ በአገሪቱ የሚመሰርቱት ስርአት ምንነት፤ ይህ ስርአት እንዴት እንደሚመጣ፤ ይህንን ስርአት ደግሞ ማምጣት የሚችለው ያ የነሱ ድርጅት ብቻ እንደሆነ ፍፁም እርግጠኞች ነበሩ፡፡ ያ የሚመሰረተው ስርአትም በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ድጋፍ እንዳለው፤ የእነሱን አመለካከት የሚቃወም ሁሉ የህዝብ ጠላት እንደሆነ ሕዝቡንም ሳይጠይቁ በእርግጠኛነት ያውቁት ነበር፡፡ የዚህ አይነት አመለካከት የበላይነቱን በያዘበት ሁኔታ እያንዳንዱ የድርጅት አባል ለድርጅቱ ያለው ፍቅርና ታማኝነት ለአገሩና ለአላማው ካለው ፍቅርና ታማኝነት ጋር አንድ ናቸው፡፡ ትግሉ ያለው በሂደት ላይ ሳይሆን በመሰረታዊ እምነት ላይ ነው፡፡ ገነትም ገነት የሚወስደው መንገድም የታወቁ ናቸው፡፡ ከዚህ የተለየ መንገድ የሚከተል በቀጥታ ሲኦል ነው የሚገባው፤ አገሩንና ህዝቡን ይዞ፡፡ ስለዚህም ባለው መሳሪያ ሁሉ ተጠቅሞ ይህንን ማስቆም ይገባል፡፡

የዚህ አይነት አመለካከት የያዘ የድርጅት አባል የራሱን ትክክለኛነት ብቻ ሳይሆን የሌላውን ድርጅት አባል ስህተት መሆን እርግጠኛ ነው፡፡ ከሌላው ድርጅት አባላት ጋር ሆኖ ተነጋግሮ የሚደረስበት ብዙ ውጤት አይኖርም፡፡ ይህ ደግሞ በተለያዩ ድርጅቶች የተቆመለት አላማ ተቀራራቢ መሆኑም ብዙ ለውጥ አያመጣም፡፡ እንደማንኛውም የቀኖና ክርክር ትንሹዋም ልዩነት በጣም የገዘፈ ሆና መቅረቡዋና ለሞት ሽረት ትግል ምክንያት መሆኑዋ አይቀሬ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ በተለይ የርዕዮተ አለም ልዩነቱ ለብዙሀኑ ህዝብ በደንብ የሚገባ ሳይሆን ሲቀር ድርጅቶች በአብዛኛው ትኩረታቸው እራሳቸውን ከሌላው የሚለዩበትን መንገድ ማፈላለግና ይህ ልዩነታቸውም በህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ዋና የእንቅስቃሴአቸው ትኩረት ይሆናል፡፡ በምንም አይነት ሊያጣሉ የማይገቡ የቃላት ልዩነቶች በድርጅቶች መሀከል ያሉ ልዩነቶችን ማጦዣ ሆነው በስራ ላይ ይውላሉ፡፡ በላብ አደርና በወዝ አደር፤በእናሸንፋለንና በእናቸንፋለን መሀከል የነበሩት ስሜት ቀስቃሽ ልዩነቶች በጊዜው የነበርነው ወጣቶች የምናስታውሰው ነው፡፡ ይህ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው ሀይል የሚቃወሙትን ሀይሎች ለመከፋፈልና በተናጠል ለማጥፋት ይጠቀምበታል፡፡ ከዚያም አልፎ ግን እየከረረ ሲመጣ በጣም በቀላሉ ወደ እርስ በእርስ መጠፋፋት መውሰዱ አይቀርም፡፡ ትንሽ የሚለኩሰው ነገር ነው የሚፈልገው፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ደግሞ የሚለኩስ ክብሪት እጥረት ኖሮት አያውቅም፡፡ በተጨባጭ የዚያን ውጤት አስከፊነትና በአገር ላይም ሊፈጥር የሚችለውን አደጋ ደግሞ በጊዜው በደንብ አይተነዋል፡፡

---

[4] ይህ ማለት በመከራ ጊዜ ድርጅታቸውን አልፎም አገራቸውን ከድተው ለፖለቲካ ባላንጣቸው ያደሩ ምንም አልነበሩም ማለት አይደለም፡፡ የዚህን አይነት አሳፋሪ አድር ባዮችም የአገራችን የቀድሞውም የቅርቡም ፖለቲካ አሳይቶናል፤ ምንም እንኳዋን የቀድሞው እንደዚህ እንደአሁኑ አይነደረቅነት የተጠናወተው ባይሆንም፡፡ በብዛት ያየነው ግን ከፍተኛ ታማኝነት የታየበት የጀግንነት ታሪክ ይመስለኛል፡፡

ከዚያም በላይ በድርጅቱ የሚመሰለው አመለካከት ዝም ብሎ በጊዜው ፖለቲካ ላይ የሚያተኩር እንደ ፖለቲካ ማህበረሰብ የጋራ ህይወትን የሚመለከት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ርእዮተ አለምን ያካተተ ስለሆነና ይህም በግለሰብ ደረጃ አለምን የምንመለከትበትን ድባብ በሙሉ ስለሚያካትት ግለሰቦች ከድርጅታቸው የሚያገኙት በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መቡዋደንን ብቻ ሳይሆን ጉዋደኝነትን፤ አልፎም ማህበራዊ ግንኙነትን ባጠቃላይ ደግሞ ከመጠን ሲያልፍ የማንነት መገለጫም ተደርጎ ነው። በሌላ አነጋገር ድርጅቶች የግለሰቡን ማንነትም ነው የሚበሉት። ስለዚህም ታማኝነቱ በጣም ጠንካራና በአብዛኛው ግለሰቡን ከድርጅቱ፤ የድርጅቱን ጥቅም ከሀገር ጥቅም ትንሽም ቢሆን ለይቶ ሊያሳይ የሚችል ክፍተት የለውም። የዚህ አይነቱን ታማኝነት ያመጣው በጊዜው የነበረው የትግል አይነት ነበር ወይንስ በጊዜው የተፈጠሩት ድርጅቶች አይነት? ወይንስ ከዚያም በላይ በአጠቃላይ በአገራችን የነበረው ባሕላዊ እሴት ከዚህ የተለየ የታማኝነት እሳቤ ሊፈጥር አይችልም ነበር የሚሉትን አስፈላጊ ጥያቄዎች ለጊዜው ትተን በጥቅሉ ልንስማማ የምንችለው ግን በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ልናሰፍር የምናስበው ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ከዜጎች የሚጠይቀው ታማኝነት ከዚህ የተለየ በመሆኑ ላይ ብዙ የምንከራከር አይመስለኝም። ይህ ግን ለምን እንደሆነ በአጭሩ ለማሳየት አሁን ያለንበት የፖለቲካ ትግል ከዚህ በፊት ከነበረው የተለየ የሆነበትን ነጥቦች በአጭሩ መጥቀሱ ውይይታችንን ያዳብረዋል ብዬ አስባለሁ።

## የአሁኑ ወቅት ፖለቲካ ከዚህ ቀደሙ በምን ይለያል?

በአሁኑ ጊዜ የበላይነትን ይዞ የመጣው ፖለቲካ በ60ዎቹ ከነበረው ፖለቲካ ጋር ሲወዳደር የሚለይበት ብዙ መሰረታዊ የአመለካከትና የተግባር ጉዳዮች አሉ። እነኝህ ልዩነቶች በመጀመሪያ በትግሉ ምንነት ላይ ያተኮሩ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የሚደረገው ትግል የዴሞክራሲያዊ ስርአት የመመስረት ትግል ነው። የዴሞክራሲያዊ ስርአት የፍልስፍና መነሻ ደግሞ ለህብረተሰቡ አጠቃላይ ጥቅም ከራሱ ከህብረተሰቡ ውጪ የሚያውቅለት፤ ልዩ እውቀት ያለው ሰው ወይንም ቡድን የለም፤ ስለዚህም የጋራ ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ለመወሰን የሚችለው ሕዝቡ ራሱ በነፃ ፍላጎቱ የሚመርጠው ሰው ወይንም የሰዎች ስብስብ (ድርጅት) ነው ብሎ ይጀምራል። ዲሞክራሲ እነኝህ ሰዎች የሚወስኑት ውሳኔ ትክክል ነው፤ ወይንም የጋራ ጥቅማቸውን የሚጎዳ ሊሆን አይችልም የሚል ግብዝነት የለውም። ከስር መሰረቱ ይህ አመለካከት በጥርጣሬ የታጠረ ነው። እንደሌሎቹ ርእዮተ አለሞች ፍፁም እርግጠኛነትን የተላበሰ አይደለም። የሰዎች ፍላጎት እንደ ሁኔታው ሊቀየር እንደሚችል፤ ዛሬ ትክክል የመሰለ ነገር ነገ የተሳሳተ ሊመስል እንደሚችል፤ ዛሬ የሚያምር የመሰለን ነገር ነገ አስቀያሚ ሊመስለን እንደሚችል (ዛሬ ቤል ቦተም ለብሶ የሚሄድ ሰው ሊሳቅበት እንደሚችል ማለት ነው) ይገነዘባል። ስለዚህም እንደ ግብ የሚወስደው የሚደረስበት ፍፁም እውነት ወይንም ምድራዊ ገነት አለ ብሎ አይጀምርም።

በዚህ አይነት የአመለካከት ምህዋር ውስጥ አጠቃላይ ማህበረሰብን በተመለከተ ሊደረስበት ይገባል ተብሎ በማህበረሰቡ በሙሉ ተቀባይነትን ያገኘ ማህበረሰባዊ ግብ የለም ማለት በማህበረሰቡ ውስጥ ለአብሮ መኖር ዋልታ የሆኑ ሁሉም ሊቀበላቸው የሚገቡ እሴቶች የሉም ማለት አይደለም። እነኝህ እሴቶች ግን በዋናነት የመጨረሻ ማህበራዊ ግብን የሚያመለክቱ ሳይሆኑ ማህበረሰቡ በጋራ ለመኖር በውስጡ ያሉትንና መቼም የማይቀሩትን የተለያየ ደረጃ ያላቸው ልዩነቶችና ቅራኔዎች የሚፈታበትን ስልትና ሂደት የሚመለከቱ ናቸው። በዚህ ሁኔታ የማይነቃነቅ መትከል ሆኖ ሊወሰድ የሚችለው የጋራ ውሳኔዎችና የግል ውሳኔዎችን መለየት፤ ይህን ከለዩ በሁዋላ ደግሞ የጋራ ውሳኔዎች የሚባሉትን እንዴት እንደሚሰጡና እንዴት ተቀባይነት እንደሚያገኙ መወሰን ናቸው። የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ የምንለውም ይህንን የአካሄድ ሂደት ነው።

ይህ በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ በመርህ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ የፖለቲካ ስርአት በአጭሩ የሚለው እያንዳንዱ ሰው እንደ ሰውነቱ፤ ቀጥሎም እንደ ዜግነቱ ማንም ሊወስድበት የማይችል (በአብዛኛ ህዝብ ውሳኔም ቢሆን) መሰረታዊ መብቶች አሉት፤ በጋራ ህይወት ውሳኔ ላይ ሁሉም እኩል ድምፅ ያለው ሆኖ፣ የጋራ ህይወታችንን የሚያስተዳድረው መንግስት የሚባለው ተቋዋም የህዝብ ውክልና ያለው በህዝብ የተመረጠ ብቻ ይሆናል። ከዚያ ውጪ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል ምንም አይነት መንግስት የለም። በፈጣሪ እንኩዋን

የተመረጠ ቢሆን። ፈጣሪ እንኩዋን በአጋጣሚ የመረጠው ካለ ይህንን ሊነግረን የሚችለው በህዝቡ በኩል አድርጎ ብቻ ነው። ይህ የህዝብ ምርጫ ግን እውን እንዲሆን፤ ምርጫው ከማንኛውም ተፅእኖ ነፃ እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑ መሙዋላት ያለባቸው ነገሮች አሉ። ህዝቡ የሚፈልገውን ለመምረጥ የሁሉንም ተፎካካሪዎች አላማና ፖሊሲ በተቻለ መጠን በእኩልነት ለመስማት መቻል አለበት። ተፎካካሪ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያለምንም ተፅእኖ ህዝቡን ስለአላማቸው ለማስተማር መቻል አለባቸው፤ ይህን ለማድረግ ዜጎች መሰረታዊ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበርላቸዋል፤ ስለዚህም የሚፈልጉትን ያለ ፍርሀትና መሸማቀቅ ለመምረጥ ይችላሉ…ወዘተ። ዜጎች መራጮች ብቻ ሳይሆኑ ተመራጮቹም እነሱው ናቸው። ከዚህ ሂደት በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ዜጋ ማህበረሰቡ በጋራ የሚሄድበትን መንገድ ለመቀየስ ተመሳሳይ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር ሆኖ የመደራጀት፤ ተደራጅቶም በፖለቲካ ሂደቱ ውስጥ የመሳተፍ መብት አለው። ከእዚህም መብት በተጨማሪ እንዲሳተፍም ይጠበቅበታል። የጥሩ ዜግነት ምልክትም ሆኖ ይወሰዳል። ያለመሳተፍ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ባለመሳተፉ ለሚወሰዱ ውሳኔዎች እኩል ተጠያቂ ነው። በዚህ ሁኔታ አንድ ዜጋ በአመለካከት ይቀራረቡኛል ከሚላቸው ሰዎች ጋር መቡዋደኑ፤ በድርጅት ተቡዋድኖም በሚሰራበት ጊዜ ከድርጅት ጉዋዶቹ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አልፎም ወዳጅነት መመስረቱ የሚጠበቅና ተገቢም ነው። ስለዚህም በአመለካከት አንድነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የድርጅት ታማኝነት ይኖረዋል። ድርጅቱ በውድድር እንዲያሸንፍ ይፈልጋል፤ ለዚያም ጠንክሮ ይሰራል። እሱ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ ህዝብ አስተምሮ ለመመረጥ የሚሞክረው በህብረሰቡ ውስጥ በተደረሰው የዴሞክራሲ ሂደት ስምምነት መሆኑን ስለሚገነዘብ እሱ እንዲከበሩለት የሚፈልጋቸው መብቶች ለሱ ባላንጣዎችም መከበር እንዳለባቸው ያምናል። እሱ ወይንም ድርጅቱ የሌሎቹን መብቶች እስከረገጡ ድረስ እሱም የቆመበት መሬት ምንግዜም ሊከዳው እንደሚችል ስለሚያውቀው በራሱ ጉዋደኞችም ሆነ በድርጅቱ እነኝህ መብቶች በፖለቲካ ባላንጣውም ላይ እንኩዋን ቢሆን እንዲረገጡ አይፈቅድም። በሌላ አነጋገር የድርጅት ታማኝነት እንዳለ ሆኖ ከድርጅቱም በላይ ያለው ከፍተኛው ታማኝነት ይህንን የጫወታ ህግ ለሁሉም በእኩልነት እንዲሰራ ላስቀመጠው የፖለቲካ ስርአት ይሆናል። የድርጅቱ አባሎች ድርጅቱን የተቀላቀሉት በፈቃደኝነት፤ አላማው ለእምነታቸው የሚጠጋ ሆኖ ስላገኙት ስለሆነ፤ በአንድ ምክንያት ወይም በሌላ ድርጅቱ ከዚህ ካመኑበት መንገድ ካፈነገጠ ድርጅቱን ለመልቀቅ፤ ወይንም ሌላ ይቀርበናል የሚሉት ድርጅት ለመቀላቀል የሚያግዳቸው ነገር የለም። በዚህም ምክንያት በዚህ በአዲሱ ፖለቲካ በግለሰቡ በራሱ፤ በድርጅት ታማኝነቱና የጨዋታው ህግ በሚያንፀባርቀው የፖለቲካ ማህበረሰብ (አገር) መሀከል የመንቀሳቀሻ ክፍት ቦታ አለ። ከላይ እንደጠቀስኩት ርዕዮተ አለም ላይ እንደታጠረ ፖለቲካ የተዘጋ አይደለም። ለዚህም ነው ስኮት ማክሊላን ዋናው ታማኝነቴ ለእውነትና ለአሜሪካን ህዝብ ነው የሚለው በሪፑብሊካን ፓርቲው ባለሙዋሎችም ዘንድ ሊተች ያልቻለውና እንዲያውም ለምን ቀድመህ ሁኔታው ሲፈጠር አልተናገርክም ወደሚለው መከራከሪያ የዞረው።

## አሁን ባለንበት የትግል ወቅት ሊኖር የሚገባን ታማኝነት ለማን ነው?

ከላይ በግርድፉ የጠቀስኩት የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ምንነት ላይና እሱም የሚጠይቀው የታማኝነት አይነት ላይ ትንሽም ቢሆን ስምምነት ካለን አሁን በአገራችን ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል ምንነትና ይህም የሚጠይቀውን ታማኝነት ደግሞ በአጭሩ መመልከት እንችላለን። አሁን ያለንበት ትግል በጥቅሉ ብናቀርበው በ60ዎቹ የነበረው የርዕዮተ አለም ትግል የከሰመበት፤ ነገር ግን ጊዜው የሚጠይቀውና አብዛኛው የማህበረሰባችን አባላት የሚፈልጉት ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሌለበት፤ በአንድ በኩል ስልጣንን በጉልበቱ ይዞ ለርዕዮተ አለምም ሳይሆን እንዲያው ጉልበት ስላለኝ ብቻ ከስልጣኔ አልወርድም፤ የህዝቡም ይሁንታ በስልጣን ለመቆየት አያስፈልገኝም ብሎ በአይን አውጣነት አገሩንና መላውን ማህበረሰብ እያመሰ ያለ መንግስት ያለበትና፤ በአንፃሩ ደግሞ አዲሱን አይነት በዜጎች መብትና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት መመስረት አለበት ብለው በሚያምኑ ግን የፖለቲካ ስልጣኑን ይዘው በተግባር የሚያውሉት ፖሊሲዎች ላይ ልዩነት ሊኖራቸው የሚችል የተለያዩ የፖለቲካ ሀይሎች ለየብቻቸው አነሰም በዛም የተናጠል (ብዙ ጊዜም እርስ በእርስ የመናቆር) ትግል የሚያደርጉበት ሁኔታ ነው። ይህ የተናጠል ትግል

ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ከሚታገሉት (ስለዚህም በአዲሱ ፖለቲካ ዋና ጥያቄ ላይ ተቀራራቢ አቋዋም ካላቸው) ሀይሎች ይልቅ ዴሞክራሲን ለማፈንና ይህ ስርአት በፍፁም በአገራችን መቆሚያ እንዳያገኝ ሌት ተቀን የሚሰራውን የነመለስን መንግስት እውነተኛ አቅሙ ከሚመጥነው በላይ በስልጣን እንዲቆይ እንዳገዘው ብዙ አያከራክርም። ጥያቄው ያለው ይህ ለምን ሆነ? ለምንድን ነው በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ እናምናለን የሚሉት ብዙሀኑ የፖለቲካ ሀይሎች ተባብረውና ተጋግዘው ሁሉም የሚስማሙበትን የፖለቲካ ጨዋታ ሕግ በአገራችን ምድር ማስቀመጥ ያቃታቸው? የሚለው ነው። ይህ ደግሞ አንድ ምክንያት ሳይሆን ብዙ ምክንያቶች ይኖሩታል። ከነዚህ ውስጥ ግን ዛሬ የምንወያይበት የታማኝነት ጥያቄ የራሱ የሆነ ድርሻ እንዳለው አሌ ማለት አይቻልም። ይህ ግን በራሱ ሁለት ተያያዥነት ያላቸው ምክንያቶች ያሉት ይመስለኛል። በድርጅቶች መሀከል ያለው ከፍተኛ የመጠራጠር ስሜትና በድርጅት አባሎች ውስጥ ያለው ከፍተኛ የታማኝነት ስሜት። ትንሽ ለማብራራት ልሞክር።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ከፍተኛ ያለመተማመንና የመጠራጠር ስሜት ይንፀባረቅባቸዋል። ያለመተማመኑ አንዱ ምንጭ የግንዛቤ ልዩነት ያመጣው ይመስለኛል። አንዳንድ ድርጅቶች ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ማለትም ለሂደቱ እምብዛም ክብር የላቸውም። ስለሂደቱ የሚያወሩት ዋናውን እምነታቸውን (ለምሳሌ ብሄረተኝነት) በተግባር ለማዋል እስከጠቀማቸው ድረስ እንጂ ለሂደቱ ለራሱ ከፍተኛ ወገንተኛነት አይሰማቸውም። ይህ እስከሆነ ድረስ ዋና እምነታችን ነው ብለው ከሚያምኑት ጉዳይ ጋር የሚቃረን እምነት ያለውን ሁሉ ይጠራጠራሉ፤ አልፈውም እነኝህ ሀይሎች የዴሞክራሲያዊው ሂደት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው ብለው አያምኑም። በሌላ አነጋገር የእነሱ እምነት ከሌላው እምነት ጋር በእኩልነት ለህዝብ ቀርቦ ቢወሰን እነሱ የሚፈልጉት ነገር መምጣቱን እርግጠኛ እስካልሆኑ ድረስ እንዲህ አይነት የጨዋታ ሕግ ውስጥ መሳተፍን አይፈቅዱም። ይህ አመለካከት ደግሞ በሌሎች የፖለቲካ ሀይሎች በኩል የእነሱን ለጨዋታው ሕግ የመገዛት ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል፤ በዚህ ሁኔታ በጋራ የሚታገሉበት ምክንያት ከነጭራሹ ይጠፋል። እንዲያውም ዋና ትኩረታቸው ማን ነው ቀድሞ ስልጣኑን የሚይዘው የሚለው ጥያቄ ላይ ይሆናል። ቀድሞ ስልጣኑን የያዘው ደግሞ ሌላውን ለማጥፋት ወደ ሁዋላ አይልም የሚል ጥልቅ ጥርጣሬ ውስጥ ሁሉንም ይጨምራል። ይህ መሰረታዊ ልዩነት ነው። ዴሞክራሲ ማለት የጨዋታው ሕግ እስከሆነ ድረስ በዚያ ሕግ ላይ ሳይስማሙ ከላይ የጠቀስኩትን አይነት አዲስ ፖለቲካ ማካሄድ አይቻልም። የጨዋታውን ሕግ ከምር የማይወስዱትን ከእንዲህ አይነት ለጨዋታው ሕግ ከሚደረግ የጋራ ትግል ብናወጣቸውም ግን በሌሎቹ መሀል ያለውን የጥርጣሬ ምክንያት በሙሉ አጠፋነው ማለት አይደለም።

የዴሞክራሲያዊ ስርአትን ምንነት በደንብ ተገንዝበውና አምነውበትም ግን ሌሎች የፖሊሲ ልዩነቶችን ከዚህ ስርአት መፈጠር ጋር በማምታታት በተለይም ደግሞ ይህ ስርአት በሁለት እግሩ እስከሚቆም ድረስ የግድ የሚኖረውን የሽግግር ሂደት እንዴት እንወጣዋለን ከሚልና በዚህ ጊዜ ወደ ስልጣን የሚጠጋው ሀይል አንዴ ስልጣን ላይ ከወጣ በሁዋላ ሌሎቹን ወጊዱ ብሎ የራሱን አምባገነንነት ሊፈጥር ይችላል፤ እንዲህ አይነትን የሽግግር ሂደት በታማኝነት ሊሰራ የሚችል ከኔ በቀር የለም፤ ስለዚህም የዚህ የሽግግር ወቅት ፖለቲካን እኔ እስካልተቆጣጠርኩት ድረስ ከታሰበበት ቦታ አይደርስም ከሚል እምነት ተባብሮ ለመታገል በተግባር የሚከብድባቸው ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። ይህ የስልት ጥያቄና አመለካከት የበለጠ ስር እየሰደደ ሲሄድ በድርጅቱ ውስጥ ያሉት አባሎችንም አመለካከት ይጣባና ሌሎች ድርጅቶችን የመጠራጠርና ሲያልፍም የመናቸፍ ሁኔታ ይፈጥራል። ከዚያም በላይ ግን በሁሉም ዘንድ የራስን ድርጅት የማስቀደም ያልሆነ ውድድር ውስጥ ይገባና በዋናነት ሁሉም የሚስማሙበትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በጋራ የማቆም ሂደት ያስረሳዋል ወይም ያጨናግፈዋል።

ይህ ጥርጣሬ መኖሩ ላይ አይደለም ያለው ችግር። እንዲህ አይነት ጥርጣሬን ሊያስወግዱ የሚችሉ የጋራ ተግባራዊ መፍትሄዎች መንደፍ ሲቻል አቅምን በእንደዚህ አይነት ትርፋማ ድካም ላይ ከማዋል ይልቅ ዋና ኢላማውን በሚያስት አልባሌ ክርክርና ጭቅጭቅ ላይ እንዲጠፋ ያደርገዋል። ይህን ሁኔታ ግን በብልህነት ካሰብንበት ለዋናው አላማ አብሮ መታገልን ሊከለክለን ልንፈቅድለት አይገባም። እንዲህ አይነት ሁኔታ ላይ ውይይቱ ጤነኛ መስመር እንዲይዝ በሁሉም ድርጅቶችና በድርጅት አባሎች ዘንድ ሊያዝ የሚገባው ግንዛቤ

ሁለት አይነት ይመስለኛል፡፡ የመጀመሪያው ዴሞክራሲ የሚያተኩረው ሂደቱ ላይ መሆኑን የተቀበሉ ሀይሎች አሁን በኢትዮጵያችን የሚደረገው የመጀመሪያው ትግል ይህን ሂደት ተግባራዊ በማድረግ ላይ የታጠረ እንደሚሆንና ከዚህ ሂደት ውጪ ያሉትን እምነቶቻቸውን ሂደቱን ተጠቅመውና ህዝቡን አሳምነው ብቻ በስራ ላይ ሊያውሉ የሚችሉ መሆናቸውን፡፡ ከዚህ ውጪ ሌላ አላማቸውን በተግባር ሊያውሉ የሚችሉበት ምንም መንገድ እንደሌለ መቀበልና ይህ ደግሞ በሂደቱ መኖር የሚስማሙ ሀይሎችን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን ማመን፡፡ ይህ እምነት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አብሮ የሚያሰራ በቂ እስትራቴጂያዊ ምክንያት መሆኑን ካመኑ በሁዋላ፤ እስከዚያ የሚያደርሰው  የሽግግር ጊዜ የስልጣን ጥያቄን ስርአቱ ከተፈጠረ በሁዋላ በሚደረገው ምርጫ ማንንም ድርጅት በተለየ እንዳይጠቅም ለማድረግ የሚያስችሉ ተጨባጭ መከላከያ እርምጃዎች ላይ መስማማት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በሽግግሩ ወቅት የሚኖረውን የስልጣን ክፍፍል በጣም በትኖ ማንም ድርጅት ጫና የሚፈጥር ስልጣን እንዳይኖረው ማድረግ ይቻላል፡፡ ወይም ደግሞ በሽግግሩ ጊዜ የመንግስት ስልጣንን ይዞ ምርጫውን የሚያካሂደው ሀይል ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጪ ያለ በቴክኒክ ችሎታው የተመረጠ የቴክኖክራቶች ቡድን አድርጎ ይህ ቡድን በመጀመሪያው ምርጫ ወቅት ምንም አይነት የፖለቲካ ስልጣን ውድድር ውስጥ እንዳይገባ ማገድ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይም በሽግግሩ ወቅት ከሚኖሩት ሀይሎች ውስጥ በምርጫው ላለመወዳደር የወሰነውን አንድ ሀይል የሽግግሩን ወቅት የፖለቲካ ሀይል እንዲይዝ ማድረግ ይቻላል፡፡ የዚህ አይነትና ሌሎችም ብዙ አማራጮች መመልከት ይቻላል፡፡ ዋናው ነጥብ ግን በሽግግር ጊዜ ሊፈጠር የሚችል የፖለቲካ ስልጣን ክፍፍልን በመፍራት ወይንም በዚህ ምክንያት በሚፈጠር መጠራጠር ምክንያት ለዋናው ትግል አስፈላጊ የሆነውን የትብብር ስራ ከመስራት መታቀብ የለበትም፡፡ ይህን ማድረግ ከተሳነን ወርቁን ሁሉ በአንድ ጊዜ ካላገኘሁ ብሎ ወርቅ የምትቀፈቅፈውን ዶሮ እንደገደለው አይነት ድንቁርናና ገብጋባነት በጋራ የተጠናወቱት ሰው ነው የሚያደርገን፡፡

እንዲህ አይነት ስልታዊ የተግባር እርምጃ በመውሰድ የጥርጣሬ መሰረቱን ማጥፋት የሚቻል ከሆነ እንዲህ አይነቱን መንገድ ድርጅቶች እንዲወስዱና ዋናው የትግል ኢላማ ላይ በማተኮርና በመተባበር የነመለስን አይን ያወጣ አምባገነናዊ ስርአት አገሩን ሁሉ ሸጠው ከመጨረሳቸው በፊት ለማስወገድ እንዲቻል የድርጅት አባሎችና በተለይም ደግሞ የድርጅት ደጋፊዎች ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና ምን ይሆናል የሚለውን በመጨረሻ በአጭሩ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ነው የታማኝነትን ጥያቄ በቀጥታ በውይይታችን ውስጥ የሚዶለው፡፡

ምንም እንኩዋን የፖለቲካ ጉዳይ በተፈጥሮው ሁሉንም የአንድ አገር ዜጋ የሚመለከት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አብዛኛው ሰው ፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ በቀጥታ ለመሳተፍ እንደማይፈቅድ ይታወቃል፡፡ እንኩዋን ፖለቲካ ራሱ ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችልበት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ሁዋላ ቀር አገርና በፖለቲካ እምነት ምክንያት በግለሰቡ ላይ ምንም ይህ ነው የሚባል አደጋ እንደማይደርስበት የታወቀባቸው፣ የዴሞክራሲ ስርአት ስር በሰደደባቸው አገሮችም በቀጥታ በፖለቲካው ውስጥ በተደራጀ መልኩ የሚሳተፈው ሰው ከአጠቃላይ ከህዝቡ ብዛት አኩዋያ ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡ በተደራጀ ፖለቲካ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች የሚሳተፉበት ምክንያትም የተለያየ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባበበባቸው አገሮች ውስጥ በፖለቲካው በቀጥታ የመሚሳተፉት  አንድም ፖለቲካን እንደ ሙያቸው የወሰዱ ሰዎች፤ (በተለምዶ ፖለቲከኞች የሚባሉት[5]) ወይም ከፍተኛ የሲቪክ ግዴታ የሚሰማቸውና ዜግነታቸውን ከምር የሚወስዱ ሰዎች፣ አለያም ከፖለቲካ የተለየ ጥቅም አገኛለሁ ብለው የሚያስቡ አድር ባዮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻው የጠቀስኩዋቸው አይነት ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚከተሉት ለማሸነፍ ትልቅ እድል ያለው ማን ነው የሚለውን

---

[5] እዚህ ላይ ፖለቲከኛ የሚለውን የተጠቀምኩበት በምርጫ ተወዳድሮ በተለያየ ደረጃ በሚገኝ የስልጣን እርከን ውስጥ ገብቶ ለመስራት የሚፈልገውን ሰው ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ዜጎች በፖለቲካ ውስጥ አንድም የአንድ ፖለቲካ ፓረቲ ቀጥተኛ ተሳታፊ አባሎች (party activists) ወይንም ደግሞ እንዲሁ በምርጫ ጊዜ ብቻ በመሳተፍ የዜግነት ግዴታቸውን የሚወጡ መራጮች ይሆናሉ፡፡ ይህንንም ትንሹን የዜግነት ግዴታ እንኩዋን ለመወጣት የማይችሉ፤ በተለያየ ምክንያት ይህንን የዜግነት መብታቸውን የማይጠቀሙ ግዴታቸውንም የማይወጡ ደንታ ቢሶች በብዛት መኖራቸው አይካድም፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለረጅም ጊዜ በቆየባቸው አንዳንድ አገሮች የዚህ ህዝብ ቁጥር ከህዝቡ ከግማሽ በላይ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ለዚህ ግን አንዱና ምናልባትም ትልቁ ምክንያት ስርአቱ እጅግ ስር ከመስደዱ የተነሳ በፖለቲካ ምክንያት ስርአቱ በመሰረቱ የሚቀየርበት ሁኔታ የለም ከሚል ልበሙሉነትና በፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል ያለው ልዩነት በህይወታችን ላይ ምንም ያክል ለውጥ አያመጣም ከሚል እምነት ይመስላል፡፡

በማሸተት ስለሆነ የፖለቲካ ትግሉ አድካሚ፤ አሰልቺና ውጤቱም በፍፁም ያልታወቀ በሚሆንበት ሰአት ፖለቲካው አካባቢ አይኖሩም፡፡ በሁዋላ ትግሉ ሊያሸንፍ ተቃርቦአል ብለው በሚያምኑ ጊዜ የሚግተለተሉ ናቸውና ለዛሬ ውይይታችን በዚያ አይነት ግፊት ፖለቲካውን የሚጠጉትን ከውይይቱ ብናወጣቸው ብዙ አንጎዳም፡፡ የመጀመሪያዎቹ አይነት ፖለቲከኞችም የተረጋጋ የምርጫ ፖለቲካ በሌለበት ሁኔታ ፖለቲካን እንደ ኑሮን ማሸነፊያ ሙያ አድርገው ሊወስዱ የሚችሉ ቢኖሩም በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ለዛሬ ውይይታችን ብዙም ትርጉም የሚሰጥ አይደለምና ልንተወው እንችላለን፡፡ ስለዚህ አሁን ባለንበት አይነት የፖለቲካ ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅት የሚቀላቀሉትም ሆነ በቀጥታ የሚደግፉት በተለያየ ደረጃም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ የሲቪክ ግዴታ የሚሰማቸው፤ ዜግነታቸውን ከምር የሚወስዱ ሰዎች አድርገን ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡[6]

እንግዲህ አንድ ሰው አንድ ድርጅት ሲቀላቀል ወይም በቀጥታ (actively) ለመደገፍ ሲወስን ዋናው ግፊቱ (motivation) የሚመጣው የሲቪክ ግዴታውን ለመወጣት ከመፈለግ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ በራሱ ግዴታውን ለመወጣት ከሚሸሸው ሰው ጋር ሲመዘን የተሻለ የሞራል መሰረት ላይ ያስቀምጠዋል፡፡ ያንን ድርጅት ሲቀላቀል (ሌሎች በአማራጭነት የተቀመጡትን ድርጅቶች ትቶ) በጥቅሉ ያ ድርጅት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት የቆመ ከመሆኑ በተጨማሪ (በዚህ መለኪያ ሌሎቹም ድርጅቶች ይህንን ይቀበላሉ ብለን አምነን) ይህንን ሰው እንዲደግፈው ያደረጉት ሌሎች የፖሊሲ አቋሞች (ለምሳሌ በኢኮኖሚ ፖሊሲ) አሉ ማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ይህ ድርጅት የዚህን ሰው ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴቶች ያንፀባርቃል ብሎ አምኖአል ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ አባል ወይንም ደጋፊ ለዚህ ድርጅት የተለየ ፍቅር፤ የላቀ ታማኝነት ይኖረዋል፡፡ ይህ ደግሞ ምንም ችግር የሌለበት ጤነኛ የሆነ ታማኝነት ነው፡፡ ይህ ሰው በእርግጥም ዴሞክራሲያዊ ከሆነ ይህ የሱና የድርጅቱ የተለዩ እምነቶች የመንግስት ፖሊሲ ሆነው በተግባር ሊውሉ የሚችሉት ድርጅቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በነፃና በእኩል ሜዳ ተወዳድሮ ማህበረሰቡን አሳምኖ መመረጥ ሲችል ብቻ ነው ብሎ ይቀበላል ማለት ነው፡፡ የሱንና የድርጅቱን እምነት በጉልበት በህዝቡ ላይ ለመጫን እንደማይችል (ሌሎቹም ድርጅቶች እንደማይችሉ) ያምናል፡፡ ይህ እምነቱ ጠንካራ ከሆነ የሱም ሆነ የድርጅቱ ዋናና የመጀመሪያ ትግል የሚሆነው ይህንን ነፃና ለሁሉም ድርጅቶች እኩል የሆነ የጫወታ ሕግ በስራ ላይ እንዲውል መታገል ነው፡፡ ይህ ሕግ በተግባር እስካልዋለ ድረስ ይህ የሚያምንበት እምነቱ ምን ያክል ትክክል ቢሆን በተግባር ለመዋል የመቻል እድሉ ዜሮ ነው፡፡ በርግጥ ድርጅቱ በሆነ አጋጣሚ ወይንም በተንኮል ወይንም በጉልበት የፖለቲካ ስልጣኑን የሚይዝበት፤ ከያዘም በሁዋላ ያንን የተለየ ፖሊሲውን ተግባራዊ የሚያደርግበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ግን ይህንን ደጋፊ የሚያስደስት ሊሆን አይችልም፡፡ ዋናውን ዴሞክራሲያዊ እምነቱን አጨናግፎ በሁለተኛ እምነቶቹ ላይ የተገኘ ጊዜያዊ ድል ስለሚሆን፡፡ የጨዋታ ሜዳው ለሁሉም እኩል የሆነ ስርአት ከተፈጠረ ግን በምርጫው ባያሸንፍ እንኩዋን ዋናውን የፖለቲካ ስርአት ፍላጎቱንና አላማውን አሳክቶአል ማለት ነው፡፡ ይህ በራሱ ትልቅ ድል ነው፡፡ ከዚያም በላይ ግን እሱና ድርጅቱ የሚያምኑበትን የተለየ እምነት በተግባር ለማዋል ዛሬ ባይችል ያ የጨዋታ ሕግ እስከተከበረ ድረስ በሚቀጥለው ጊዜ ለመሞከርና ሕዝቡን አሳምኖ ስልጣን ላይ ለመውጣት እድሉ ሁሌም ክፍት ነው፡፡

የዚህ ሰው የታማኝነት ምንነትና ጥልቀት የሚፈተነው የተቀላቀለው ወይንም የሚደግፈው ድርጅት የተለየ በሚያደርጉት ሁለተኛ ደረጃ አቋሞቹ ምክንያት ከዋና የዴሞክራሲ ሰርአት መመስረት አቋሞቹ ጋር የሚፃረር ነገር ቢሰራ አባሉ ለድርጅቱ ካለው ታማኝነትና ለዋና እምነቱ ካለው ታማኝነት ሊመርጥ የሚገባው የቱን ነው የሚለው ላይ ነው፡፡ እንደዚህ በጥቅሉ ሲቀመጥ በጣም አከራካሪ አይመስልም፡፡ እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቻችሁ ያለምንም ማመንታት ለዋና እምነቱ ያለው ታማኝነት መቅደም አለበት ብላችሁ የምታምኑ ይመስለኛል፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ድርጅቱን ወይንም የድርጅቱን መሪዎች መገሰፅ፤ እንዲስተካከሉ መምከር፤ አልስተካከልም ካሉ እነሱን ለመተካት በድርጅቱ ውስጥ መንቀሳቀስ፤ ይህ ሁሉ አልሆን ካለም

[6] ይህንን ግምት በከፍተኛ ጥርጣሬ የሚመለከቱ እንደሚኖሩ እገምታለሁ፡፡ በኛም አገር አይነት ፖለቲካ ምናልባት ወደፊት ከስልጣን የሚገኝ ጥቅም ይኖራል ብለው አምነውና በጥንቃቄ አስበውበት ትግሉን የሚቀላቀሉ ሊኖሩ እንደሚችሉ ጭራሹኑ አሌ የሚባል አይደለም፡፡ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ አባሎችና ደጋፊዎች በአብዛኛው እንደዚያ ናቸው ብሎ መገመት ግን በኔ እምነት ተስፋን የሚያጨልም ተጠራጣሪነት ነው የሚሆነው፡፡

ድርጅቱን እስከመልቀቅ የሚደርስ እርምጃ መውሰድ ለአላማው ታማኝነት ያለው ሰው ማድረግ የሚጠበቅበት በጎ ነገር ይመስለኛል፡፡

ይህ ጥቅል ንድፈ ሀሳባዊ የሚመስል ምሳሌ በተግባር በአገራችን ሁኔታ ስናመጣው አንዴም ቀላል ወዲያውም የተቆላለፈ ስእል ይሰጠናል፡፡ በአገራችን በጣም አስከፊ ሊባል የሚችል ወራዳ አምባገነናዊ ስርአት አለ፡፡ ይህን ስርአት መታገልና መጣል በቦታውም ዴሞክራሲያዊ ስርአት መተካት ይገባል ብለው የሚያምኑ ግን በተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ጉዳዩች ላይ የተለያየ አቋዋም ያላቸው ብዙ ድርጅቶች አሉ፡፡ እነኝህ ድርጅቶች ለስርአት ለውጥ የሚያደርጉትን ትግል አስተባብረው ካለው ስርአት የተሻለ አማራጭ አቅርበው ቢታገሉ በዋናነት እንፈልገዋለን የሚሉትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በአጭር ጊዜ ለማግኘት፤ ከዚያም በሁዋላ ባሉዋቸው ሁለተኛ ደረጃ ልዩነቶች ላይ በነፃ ተወዳድረው ህዝብ የመረጠውን ለጊዜው ተቀብለው፤ ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ እንደገና በልዩነቶቻቸው ላይ ለመወዳደር የሚያስቸላቸውን ሁኔታ መፍጠር ይችላሉ፡፡ ይህንን ከማድረግ ይልቅ ግን በሁለተኛ ደረጃ ልዩነቶቻቸው ላይ በማተኮር የራሳቸውንም ሆነ የአገራቸውን መከራ ያራዝማሉ፡፡ ይህ ትክክል እንዳልሆነ ሁሉም የሚገነዘቡ ይመስላል፡፡ በዚህ ሁኔታ በድርጅቶቹ ውሳኔዎች ላይ በቀጥታ የማይሳተፉት ደጋፊዎች ለሚደግፉቸው ድርጅቶች ባላቸው ታማኝነት ምክንያት እንዲህ አይነቱን ትብብር ለመፍጠርና የመጀመሪያ ደረጃ ትግሉን ከዳር ለማድረስ የሚደረገውን ትግል የሚያደናቅፉትን ድርጅቶቻቸውን ከመገሰፅና ድርጅቶቹ ዋና አላማቸውን እንዳይስቱ ከመጎትጎት ይልቅ በጭፍን ድርጅቶቻቸውን መደገፍ ወደ መፍትሄው እየተጠጋን ከመሄድ ይልቅ እንድንርቅ ያደርገናል፡፡ እዚህ ላይ ነው በተጨባጭ የእያንዳንዳችን ዋና ታማኝነት ለማንና ለምን ነው የሚለውን በጥንቃቄ መመዘን የሚገባን፡፡ ያለንባቸውን ድርጅቶች መደገፍ የሚገባንን ያክል በዚህ ወሳኝ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግል ወቅት ታማኝነታችን በዋነኛነት ለእውነቱና ለዴሞክራሲ ስርአት መመስረት መሆን አለበት የምለውም ለዚህ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊው ስርአት ከተመሰረተ በሁዋላ ነፃ ምርጫና ውድድር በሚደረግበት ጊዜ ድርጅቶቻችን እንዲያሸንፉና ከላይ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጡ ያልኩዋቸውን እምነቶቻችንን የመንግስት ፖሊሲ ለማድረግ ሙሉ ጊዜያችንን ሰጥተን ብንንቀሳቀስ፤ ለዚህም ለድርጅታችን ያለንን ታማኝነት ብናፀና ተገቢ እንጂ ነው፡፡ ስለዚህ ታማኝነት ተገቢ የሞራል እሴት የሆነውን ያክል በምን ሁኔታና ለምን ጉዳይ የሚለውን ከግምት ያላስገባ ታማኝነት ግን የቆምንበትን የሞራል መሰረት የሚያናጋ ሊሆን እንደሚችል አውቀን በዝግታና በጥንቃቄ መፈተሽ ይጠቅማል ለማለት ነው፡፡

**ማጠቃለያ፡፡**

በዚህ ጉዳይ ላይ መስማማት ለትግላችን ትልቅ ፋይዳ ያለው ጉዳይ ነው፡፡ የአመለካከት ጥራት ይሰጠናል፤ የትግሉን ቅደም ተከተል ከአላማው ትልቅነት ቅደም ተከተል ጋር እንድናዋህደው ያደርገናል፤ ዋና ኢላማችንን ከሁለተኛ ደረጃ ኢላማችን ጋር ለይተን አይናችንን በዋና ኢላማችን ላይ እንድናሳርፍ ያደርገናል፤ ምንም ፋይዳ ከሌለው ጉንጭ አልፋ የእርስ በእርስ ንትርክ አውጥቶ ለዴሞክራሲያዊ ትግል የተሰለፉ ሀይሎችን በአንድ ላይ ለማስተባበርና ለማታገል፤ የትግሉን ደጋፊዎች በእጅጉ ለማስፋት ስለዚህም የትግሉን አቅም በከንቱ እንዳይባክን ለማድረግ ይጠቅመናል፤ በትግሉ ሂደት አጥብቀን ልናስብባቸውና አትኩሮት ሰጥተን ልንወያይባቸው የሚገቡ ብዙ ጉዳዮችን ዘንግተን ምንም ትርፋማ ያልሆኑ ተራ የልዩነት ወሬዎችን እያጦዝንና በነሱ ላይ ጊዜያችንን እያጠፋን ፖለቲካችንን የተመሰቃቀለ የጋራ ኑሮአችንን ማስተካከያ መሳሪያችን ሳይሆን የወሬ ሱሳችን ማስተንፈሻ ምንም ምርታማ ያልሆነ መደበሪያችን እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መስርተው በመለስተኛ ማስተካከያዎች ላይ ለሚከራከሩት የምእራብ አገሮች ፖለቲካም እንኩዋን ቢሆን ተቀባይነት የሌለው አሳፋሪ ነገር ነው፡፡ ፍፁም መብቱን ተገፎ የፍርሀትና የሰቆቃ ኑሮ ለሚኖር፤ የአገሩን መኖር አለመኖር ወይም የአገሩ ዳር ድንበር ምን እንደሆነ እንኩዋን በስልጣን ላይ ያሉ ያልወከልናቸው ትእቢተኛ ባለስልጣኖች እንደፈለጉ በሚያደርጉበት አገር፤ የአገራችን ህዝብ የእለት ተቀን ኑሮ ፍፁም እማይወጣው መራራ ሬት እየሆነበት እንደሆነ በየቀኑ በምንሰማበት አገር የዚህ አይነት መሰረት የሌለው የልዩነት ፖለቲካ ፍፁም ይቅር የማይባል አስነዋሪ ወንጀል ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ ለመውጣት ነው ሁላችንም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲታነፅ ነው ዋና አላማችን የምንል ሁሉ የታማኝነት አቅጣጫችንን ለአላማችን ማድረጋችን በከፍተኛ የሞራል መለኪያ ብናየው እንኩዋን አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

ከዚያም በላይ ግን በተግባርም ይህንን የልዩነት ፖለቲካ ከጋራ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ትግሉ አግዝፈው የሚያዩ ሀይሎችን መስመር ለማስገቢያ የድርጅት አባሎችና ደጋፊዎች ዋና ታማኝነታቸው ለዴሞክራሲ ትግሉ መሆኑን ማሳየታቸው የጋራ ትግላችንን የሚጠቅም ትልቅ እሴት ነው የምለው፡፡

ይህ ደግሞ ዛሬ ከምንዘክረው የሰማእታት ቀን ጋርም ይያያዛል፡፡ በ66 አብዮት ወቅትም ሆነ፤ በሰኔና በጥቅምት ለተሰዉት ወገኖቻችን የምናስባቸው የአንድ ድርጅት አባል ስለሆኑ፤ የሰማእትነታቸውም ፋይዳ ለነበሩበት ድርጅት ብቻ ቢሆን ኖሮ የትዝታችን ጥልቀትና የህይወታቸውም ትርጉም ለዚያ ድርጅት ወገንተኞች ብቻ ይሆን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ክብራቸውን እጅግ ያሳንሰዋል፡፡ የሞቱት ለነፃነታችን፤ ለክብራችን፤ ለአገራችን፤ ለጋራ ህይወታችን ብለው ነው ብለን ስለምናምን ነው ትልቅ ክብርና በታሪክም ትልቅ ቦታ የምንሰጣቸው፡፡ ታማኝነታቸው ለአገራችን፤ለፍትህና ለዴሞክራሲ ስለሆነም ነው ማንም ድርጅት የሱ ብቻ ሰማእታት አድርጎ እንዲያያቸው የማይቻለው፡፡ እሱማ ቢሆን ከድርጅቱ ውድቀት ጋር አብሮ ስማቸው ይሞት ነበር፡፡ ስማቸው ዘላለማዊ የሚሆነው፤ ሞታቸው ለሁላችንም ጥሩ ህይወት ብለው ስለሆነ ነው፡፡

ሁልጊዜም የኢትዮጵያ ወታደሮች ታማኝነታችሁ ለአንድ ድርጅት ወይንም ለአንድ መንግስት ሳይሆን ሁላችንንም ለሚመለከተው ለአገራችን ክብርና ነፃነት ይሁን የምንለው እኛም እንደማህበረሰብ አገራቸውን በህይወታቸው ለማገልገል ለቆረጡት ዜጎቻችን ተመሳሳይ ክብር ለመስጠት ስለምንፈልግ ነው፡፡ የደርግ ወታደሮች በህብረተሰቡ ዘንድ እንደ ጠባቂያቸው ሳይሆን እንደ በዳያቸው ስለታዩ የነመለስ መንግስት ስልጣን ላይ ሲወጣና ጦሩን በቀላሉ በትኖ የራሱን የድርጅት ጦር የአገር መከላከያ ሰራዊት ሲያደርግ በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ከንፈር መምጠጥ እንኳዋን ያልታየው ለዚህ ይመስለኛል፡፡ የአሁኑም የመከላከያ ሰራዊት የአገሩን ዳር ድንበር በደሙ ማስጠበቅ፤ ያልታጠቁ ደካሞችን ከጉልበተኞች መከላከል ሲገባው የአንድ ድርጅት አልፎም የጥቂት ግለሰቦች ስልጣን አስጠባቂ፤ የህዝብ ምርጫ ኮሮጆ ሰራቂ፤ ከድንበሩ አልፎ የጎረቤት ሀገር ደካማ ሰዎች በዳይ፤ የአገሩ ድንበር ሲደፈር ዝም ብሎ ተመልካች ሆኖ ሲቀርብ፤ በዚህም ምክንያት አገራችንን ልቀቁ ከሚሉ አማፅያን ጋር በሚያደርገው ትግል እየሞተ አስከሬኑ ሲጎተት እያዩ የአገሩ ሰዎች በአፍረት አንገታቸውን የሚያቀረቅሩበት ሁኔታ ሲፈጠር በፅኑ የተዋረደው ወታደሩ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም የአገሩ ዜጎች ነን፡፡ ለዚህም ነው የአገራችንን የመከላከያ ሰራዊት መንገድህን ቀይር፤ ታማኝነትህ ለአንድ ድርጅት ወይንም ለጥቂት ግለሰቦች መሆኑ ቀርቶ ለአገርህ ይሁን እያልን የምንማፀነው፡፡ ለዚህም ነው በተመሳሳይ የሁላችንም ዋነኛ ታማኝነት ለድርጅታችን ሳይሆን ለወገናችን፣ እኛንም ጨምሮ፣ ለአገራችን፤ ለነፃነታችን፤ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታችን ይሁን የምንለው፡፡

አመሰግናለሁ፡፡